**የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡»**

2ጢሞ. 3÷16-17




**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»**

**መዝ.** 118(119)÷130

# ማውጫ

ክፍል 3

ገጽ

ትምህርት ዐሥራ አንድ፡- የጌታ ዳግም ምጽአት ........................ 4

የጌታ ቀን ........................................................................ 4

የዳግም ምጽአቱ ምልክቶች ...................................................... 6

የጌታ አመጣጥ ................................................................... 6

ጌታ ሲመጣ ....................................................................... 6

የጌታን ዳግም ምጽአት የምንጠብቀው........................................7

ትምህርት ዐሥራ አንድ፡- የጌታ ዳግም ምጽአት ጥያቄዎች.......... 9

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና አላማ በጌታ አዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው:: «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው:: ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን::

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል:: ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቊጥር መቀበል ይኖርባችኋል:: ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ::

የመላላክ ትምህርቱ፣ አሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል:: አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው:: ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን::

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የአሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን::

# ትምህርት አሥራ አንድ፡-
# የጌታ ዳግም ምጽአት

የወንጌል እምብርት ነው ተብሎ የሚታመንበት ክፍል በ1ቆሮ. 15፥3-4 የሚገኘው ነው፡፡ ይህ ክፍል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን እንደ ሞተ፣ እንደ ተቀበረና በሦስተኛው ቀን እንደ ተነሣ ይናገራል፡፡ ከሞት የተነሣው ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ፣ ለተለያዩ ሰዎችና ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ሰዎች ታይቷል፡፡ ከትንሣኤ በኋላ ወደ ሰማይ በማረግ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፡፡

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ሰብስቦ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ለእርሱ ምስክሮች እንደሚሆኑ ከነገራቸው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ከእነርሱ ከፍ ከፍ አለ፡፡ ደመናም ተቀበለው (ማር. 16፥19፤ ሐዋ. 1፥9)፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ከእነርሱ ሲሄድ ትኩር ብለው ይመለከቱ ነበርና ነጫጭ የለበሱ ሁለት ሰዎች (መላእክት ሳይሆኑ አይቀሩም) ወደ እነርሱ ቀርበው፣ የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው (ሐዋ. 1፥11)፡፡

ኢየሱስም ገና ከመሞቱ በፊት በሊቀ ካህናቱ ፊት በቀረበ ጊዜ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ «… የሰው ልጅም … በሰማይም ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ» (ማር. 14፥62)፡፡ ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላም ሐዋርያቱ፣ ኢየሱስ ዳግመኛ እንደሚመጣ ደጋግመው አስተምረዋል፡፡ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለክርስቲያኖች ታላቅ ተስፋ መሆኑን ሐዋርያው ሲገልጽ፣ «… የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፣ …» (ቲቶ 2፥12-13) በማለት ይናገራል፡፡

## የጌታ ቀን

1. ሌባ እንደሚመጣ እንዲሁ ድንገት ይሆናል (ማቴ. 24፥43-44)፤

2. ቀኒቱና ሰዓቲቱ የታወቀች አይደለችም (1ተሰ. 5፥1፤ ማቴ. 24፥36-39)፤
3. በአንድ ጊዜ ለሁሉም ይገለጻል (ማቴ. 24፥26-27)።

## የዳግም ምጽአቱ ምልክቶች

በማቴ 24፥3-44 እና በሌሎችም ክፍሎች በተዘረዘረው መሠረት ክርስቶስ ዳግመኛ ከመምጣቱ በፊት የሚከተሉት ነገሮች ይሆናሉ፦

1. ብዙዎች እኔ መሲሕ ነኝ (ክርስቶስ ነኝ) እያሉ በክርስቶስ ስም ይመጣሉ፤
2. ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤
3. ረኃብና ቸነፈር ይሆናል፤
4. የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይከሠታል፤
5. አማኞች ይሰደዳሉ፤ እርስ በርስም ይሰጣጣሉ፤
6. በእምነት የማይጸኑና የሚሰናከሉ ይኖራሉ፤
7. ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ይነሣሉ፤ የተመረጡትንም እንኳ ለማሳሳት ድንቆችንና ተኣምራትን ያደርጋሉ፤
8. የብዙ ሰዎች ፍቅር (ከክፋት ብዛት የተነሣ) ይቀዘቅዛል፤
9. የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር ይሆን ዘንድ ይሰበካል (ማቴ. 24፥14)፤
10. እንደ ኖኅ ዘመን ይሆናል (ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ነገር ግድ የሌላቸው በመሆን የዕለት ተግባራቸውን ማከናወን ይቀጥላሉ)፤
11. በምድር ላይ የጭንቀትና የመከራ ዘመን ይሆናል (2ጢሞ. 3፥1-5፤ ሉቃ. 21፥25-26)፤
12. ምርመራና ዕውቀት ይበዛል (ዳን. 12፥4)፤
13. ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ሐሰተኛው ክርስቶስ (የጥፋት ልጅ) ይገለጣል (2ተሰ. 2፥3-4)።

ከእነዚህ ምልክቶች ገና አልተፈጸመም የምንለው ምልክት ቢኖር፣ በቊጥር 9 ላይ የተጠቀሰው ብቻ ነው ብንል ከእውነት የራቀ አይሆንም።

የእግዚአብሔር ቃል የጌታ ዳግም ምጽአት ለምን እንደ ዘገየ ሲናገር፣ እንዲህ ይላል፤ «ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።» (2ጴጥ. 3÷9)

## የጌታ አመጣጥ

1. በደመና (ማር. 14÷62)፣
2. በክብር (ማቴ. 4÷30)፣
3. ከመላእክቱ ጋር (ማቴ. 24÷31)፣
4. በእሳት ነበልባል 1ተሰ. 1÷7፣
5. በእግዚአብሔር መለከትና በመላእክት አለቃ ድምፅ ይሆናል (1ተሰ. 4÷16)።

## ጌታ ሲመጣ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡-

ሀ. ለአማኞች

1. በጌታ ያንቀላፉት አስቀድመው ይነሣሉ (1ተሰ. 4÷16)፤
2. ከዚያም ሕያዋን ሆነን በምድር የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን (1ተሰ. 4÷17)፤
3. እንዲሁም ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንሆናለን (1ተሰ. 4÷17)፤
4. ኢየሱስ ከቅዱሳኑ ጋር ለሺህ ዓመት በምድር ይገዛል (ራእ. 20÷4-6)፤
5. በቅዱሳኑ ይከበራል (2ተሰ. 1÷9)፤
6. ቅዱሳኑ ይገረማሉ (2ተሰ. 1÷10)፤
7. ቅዱሳኑ በእርሱ ይከበራሉ (2ተሰ. 1÷10-12፤ ራእ. 20÷4-6)።

ለ. <u>ሳሳመኑ</u>

1. በቀል ይፈጸምባቸዋል፤ ማለትም በጌታ ቅዱሳን ላይ ያደረጉት ክፉ ነገር ሁሉ በእነርሱ ይደረግባቸዋል (2ተሰ. 1፥7)።

2. ከእግዚአብሔር ኀይልና ክብር ፊት ይርቃሉ (2ተሰ. 1፥10)።

3. በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ (2ተሰ. 1፥6-9)።

የጌታ ዳግም ምጽአት እንዲህ ከሆነ፣ አማኞች ነቅተንና ተዘጋጅተን ልንጠባበቀው ይገባል።

## <u>የጌታን ዳግም ምጽአት የምንጠብቀው</u>

1. ኀጢአተኛነትንና ዓለማዊ ምኞትን በመካድ (ቲቶ 2፥12፤ 1ተሰ. 1፥10)፣

2. ቅኖችና አለነውር በመሆን (ፊልጵ. 1፥9)፣ «ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለ ነውር እንድትሆኑ ..»

3. ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል በመመላለስ (ቲቶ 2፥13)።

## <u>የጌታ ዳግም ምጽአት ለእኛ ለአማኞች ምን ትርጒም አለው?</u>

1. <u>ጌታ የሚመጣው የሰጠንን መክሊት እስከነትርፉ ሊወስድ ነው።</u>

የመክሊቱን ታሪክ በማቴ. 25፥14-30 ስንመለከት፣ የሦስቱ ባሪያዎች ጌታ እንደ አቅማቸው ለአንዱ 5 መክሊት፣ ለአንዱ 2 መክሊት ለአንዱ ደግሞ 1መክሊት ከሰጠ በኋላ ወደ ሌላ አገር ሄደ። ከዚያም ከብዙ ዘመን በኋላ ተመልሶ በመምጣት እንደ

ተቈጣጠራቸው እናነባለን። ሦስቱ ባሪያዎች ምን እንደ መለሱለትና ጌታቸውም ምን እንዳላቸው ከክፍሉ ማንበብ እንችላለን። እኛንስ ጌታ ሲመለስ ምን ይለን ይሆን? መክሊታችንን ቀብረን ከሆነ በጌታ ፊት የምናፍርበት ጊዜ፣ በመክሊታችን አትርፈን ከሆነ ደግሞ፣ «<u>መልካም! አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ</u>» የምንባልበት ጊዜ ይሆናል።

2. <u>ጌታ ሲመጣ የሚወስደው ተዘጋጅተው የሚጠብቁትን ብቻ ነው።</u>

«ወገባችሁ የታጠቀ፥ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ <u>እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጅን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት</u> ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ። ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው። … እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።» (ሉቃ. 12፥35-40)

በማቴ. 25፥1-13 ያለውን የአሥሩን ቆነጃጅት ታሪክ ስናነብ፣ አምስቱ ሰነፍ፣ አምስቱ ደግሞ ልባሞች እንደ ነበሩ እናያለን። ልባሞቹ ከሙሽራው ጋር ወደ ሰርግ ሲገቡ፣ አምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅት ግን ወደ ሰርጉ መግባት አልቻሉም ነበር። «<u>ተዘጋጅተው</u> የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፤ <u>ደጁም ተዘጋ</u>።» በጌታ ዳግም ምጽአትም ከእርሱ ጋር መግባት የሚችሉ ተዘጋጅተው የሚጠባበቁት ብቻ ናቸው።

ጌታን በቅድስና፣ በትጋትና በታማኝነት ስንጠባበቅ፣ ከጸጋ ስጦታዎች አንዳች አይጐድልብንም። እንዲሁም ጌታ ራሱ ለዚያን ቀን ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ እንድንሆን ያደርገናል።

«እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ፣ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጐድልባችሁም፤ እርሱም ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትሆኑ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያጸናችኋል።» (1ቆሮ. 1፥7-8)

## የጌታን ዳግም ምጽአት ሁልጊዜ ተግተን የምንጠብቅ ባሪያዎች እንሁን!

# ትምህርት አሥራ አንድ፡-
# የጌታ ዳግም ምጽአት

የመታወቂያ ቍጥር፤________________________________________

ስም፤______________________________________________

አድራሻ፤___________________________________________

1. ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት ማወቅ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

2. ጌታ ዳግመኛ ስለሚመጣበት ቀንና ሰዓት የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?

3. ጌታ ከመምጣቱ በፊት እንደ ምልክት ከሚከናወኑት ነገሮች አምስቱን ጥቀስ፡፡

4. ጌታ ዳግመኛ ሲመጣ ለአማኞች ምን ምን ይሆናል? ለማያምኑስ?

5. አንድ አማኝ የጌታን ዳግም መጽአት እንዴት መጠባበቅ አለበት»? ለምን?

6. የጌታ ዳግም ምጽአት ለአንተ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

7. ጌታ ዛሬ ቢመጣ፣ እርሱን ለመቀበል ምን ያህል ተዘጋጅተሃል?